**ባለፉት ተከታታይ ዕትሞች ፤ በዚህ ዐምድ ሥር ሲነበብ የከረመዉን ደማቁን የነጌሌ ቦረና የኢሕአፓ ወጣት ሊግ (ኢሕአወሊ) አባላት ገድል እነሆ ደመደምን ። እኛ በጽሑፍ እናስፍረዉ እንጂ ፤በዚያ ወርቃማ ትዉልድ የቆየልን አገርንና ወገንን የማፍቀር እጹብ ድንቅ የተጋድሎ ታሪክ በደምና በህይወት መሥዋዕት ደማቅ ቀለም ነዉ የታተመዉ ። ተወደደም ተጠላም ከትዉልድ ወደ ትዉልድ እየተወራረሰ ፤ ከከሃዲዎች ሁሉ ጋር በኀሊና ሸንጎ ተሟግቶ እየረታ የሚበረታ ፤ የጠራ ኢትዮጵያዊ የእዉነት መስመር ስለመሆኑ ጥርጥር የለዉም ። በዚሁ ዓላማ ጠገግ ፤ በቀጣይ ባለተራነት ፤ አገራቸዉንና ወገናቸዉን ያሉ የታላቁ የኢትዮጵያ ህዝብ ሴት ልጆች በፍቅር፤ በዉበት፤ በጠነከረ እምነትና ወኔ አስጊጠዉ ካስቀሩልን አያሌ ሕዝባዊና አብዮታዊ የተጋድሎ ታሪኮች ዉስጥ አንዱን ይዘን ቀርበናል ። ከትረካው ወጣኒነት እስከ መግቢያዉ ድረስ የድንቅ ብዕሩን ትሩፋት ላቋደሰን ደራሲ ለባቢሌ ቶላ ፤ እንዲሁም በጎደለበት ሁሉ ለሞላችሁልን የጓድ ቆንጂት ቤተሰቦች ሁሉ ምስጋናችን ይድረሳችሁ ።**

## በቀይ ሽብር የሞት ጥላ ሥር ፤
## የጓድ ቆንጂት ተከሉ ከራሞት



ትርሲት/ቆንጂት አርሶ አደሩንና ቤተሰቦቻቸዉን በማስተማር ላይ

**(ባለታሪኳ ከጻፈቸዉ ያልታተመ ማስታወሻ የተወሰደ ) ቅድመ ነገር ፤**

**( በባቢሌ ቶላ ፤ - ሰኔ ፩፱፻፹፱ ዓ.ም )**

ሁላችንም ትርሲት በሚል የትግል ስሟ ነበር የምናዉቃት ። ግዳጃችን አድርገን በወሰድነዉ በዚያ ረዥም የትግል ሂደት ዉስጥ ተሳትፎ ከነበራቸዉ ቆነጃጅት ጓዲቶች መሃከል አንዷ የሆነችዉን ወጣት ማወቅ በራሱ መታደል ነበር ። ወላጆቿ ያወጡላት ስም ቆንጂት ነዉ ፤ ቆንጂት ተከሉ ። በወቅቱ ከየአይንሸት ተፈሪ ጋር ትዳር መሥርታ ነበር ። እንደርሷዉ የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ) አባል የነበረዉን ባሏን የዐይንሸትንም ሆነ ፤ የሀገሪቱ ርዕሰ ብሔር የነበሩትን አባቱን ፤ ብርጋዴር ጄኔራል ተፈሪ ባንቴን ፤ - ( በየካቲት ፩፱፻፷፱ ዓ.ም ) - የገደላቸዉ የመንግሥቱ ኃይለማርያም አገዛዝ ነዉ ።

ትርሲት ፤ከሕዝብ ጋር ተዋህዶ የማገልገልን ትርጉም ማሳያ ተምሳሌት ነበረች ። ከጥቂት ዓመታት የመስክ ቆይታ በኋላ ከአርሶአደሩ -በተለይም ከሴቶቹ ጋር ፤ በሁለመናዋ ተመሳስላ ቁርጥ ያለች ገጠሬና አፈር ገፊ ወጥቷታል ። ለሰዓታት ከዛፍ ጥላ ሥር ሆና ንድፈ ሃሳብ የሚያስጨብጥ ዳጎስ ያለ መጽሀፍ ወይም እጇ የገባዉን ልብ አንጠልጣይ ልብ ወለድ በንባብ ፉት የማለት ችሎታ የነበራት ይህቺዉ ለግላጋና ተወዳጅ ሴት ለዛ ያለዉ ቀልድ አዋቂና ምኔም ቢሆን በገዛ ራስዋ ላይ ለመሳለቅ ወደ ኋላ የማትል ትሁት ነበረች ።

እጅጉን ማራኪ ሕይወት አሳልፋለች ። ከኢትዮጵያ ወደ መካከለኛዉ ምሥራቅ ፤ ከዚያም ወደ ዩናይትድ ስቴትስ በመሄድ የኖረች ሲሆን በኋላም ወደ ኢትዮጵያ ተመልሳለች ። መጀመሪያ ላይ ፤ ስለገዛ ህይወቷ መጽሐፍ እንድትጽፍ ላቀረብኩላት ሃሳብ መልሷ ፈጽሞ እንቢታ ነበር ።ሆኖም መጽሐፉ ወጣት ልጃገረዶችን በማነቃቃት ትግሉን እንዲደባለቁ ለማድረግ ጠቀሜታዉ የላቀ መሆኑን በማሳሰብ ጎተጎትኳት ። እናም ተስማማች ። የመጽሐፉን ቢጋር በጋራ ሆነን በሰባት ምዕራፎች በመከፋፈል ነደፍነዉ ። በይዘቱም የርሷን ህይወት እየተረከ ትግሉ በአንዲት ታጋይ ሴት ሕይወት ዉስጥ የሚኖረዉን አንድምታ እንዲያንጸባርቅ ተለምነዉ። “ሙታንታ ታጣቂይቱን በጥይት በሏት /” የሚል ጊዜያዊ ርዕስም ሰጠነዉ ።

ትርሲት ግና ፈጽሞዉኑ መጽሐፍ ለመጻፍ የሚበቃ ፋታ አልነበራትም ። በኋላ ላይ በወያኔ ጦር ተይዘዉ ደብዛቸዉ ከጠፋዉ ፤ ስጦታዉ ሁሴንን ፤ በለጠ አምሐንና አበራሽ በርታን ከመሳሰሉ ሌሎች ጓዶቿ ጋር ፤ በኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ሠራዊት (ኢሕአሠ)፤ የፖለቲካ መምሪያ ሀላፊ ሆና በማገልገል ላይ ነበረች። ወጣት ተዋጊዎችን ፤ አርሶ አደር ሴቶችንና አዛዉንቶችን ታስተምራለች ። እናም ቃል ሊገልጸዉ ከሚችለዉ በላይ ሁሌም በሥራ የተጠመደች ባተሌ ነበረች ። የድርጅቱን መሪዎችና ተዋጊዎች የበለጠ በሥራ እንዲተጉ አዘዉትራ ትነዘንዝ -ትነዘንዝ -ትነዘንዝ ነበርና “ነዝናዚት” በሚል ቅጽል ስም እንጠራት ነበር ። ከራሷ በላይ ለሌሎች የምትጨነቅ ፤ እጅጉን ሰዉ ወዳድ የመሆኗን ያህል ሞራልን በማነቃቃት ረገድ ከቶ ወደር አልነበራትም ።

# ትናንትና

ህዳር ፱ ቀን ፩፱፻፹፰ በጻፈችልኝ ደብዳቤ ፤ ፋታ በማይሰጠዉ የዘለዕለት የሥራ ክንዋኔዎቿ ጣልቃ እያስገባች ፤ ጥቂት ገጾች ያህል የጻፈች መሆኑን ገለጸለችልኝ ። “ጥቂት” የተባለዉ ፤ ከድካሟ አረፍ ልትልበት ይገባ በነበረ ደረቅ ሌት ፤ በላምባ መብራት እየታገዘች ፤ አራት ደብተሮች በፈጁ አንድ መቶ ሰባ ሁለት ገጾች ላይ ያሰፈረችዉ የእጅ ጽሁፏ ነበር ። አዲስ አበባ ዉስጥ፤ በፋሺስቱ አገዛዝ እጅ ወድቃ ፤ ከመገደል ለጥቂት የተረፈችበትን የዘመነ ቀይ ሽብር ተሞክሮዋን አስፍራበታለች ።...... “ ይኼ የመጀመሪያዉ ነዉ...... ፤” በማለት ስለቀጣይነቱ ቃል ገብታ የነበረ ቢሆንም ፤ ሰባት ምዕራፍ ያለዉ መጽሀፍ ለማዘጋጀት በጋራ የወጠንነዉን ዕቅድ ከዳር ለማድረስ የሚያስፈልገዉን ያህል በቂ ጊዜ ለማግኘት ፈጽሞ አልተቻላትም ።

የትርሲት ታሪክ ፤ ባልተሟላ መልኩም ቢሆን እንኳ፤ አሁኑኑ ሊነገር የሚገባዉ ነዉ ። ከልቧ የምትወድደዉና ሕይወቷን የሰጠችለት ድርጅቷ ፤ የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ( ኢሕአፓ) ፤ ዛሬም ከተነሳበት ዓላማ ዝንፍ ሳይል ፤ ለኢትዮጵያ ሕዝብ የሥልጣን ባለቤትነት መረጋገጥ ለአራት አሥርት ዓመታት ያደረገዉን ትግል በጽናት ገፍቶበታል ። ጽንሰ ሃሳቡን በወግ ለተነተነዉ ፤ ዞሮ ዞሮ ማንኛዉንም አብዮት የሚያንቀሳቅሰዉ ሞተር “ ፍቅር” መሆኑን ጠንቅቀዉ ከተገነዘቡት ጥቂት ጓዶች መሃከል አንደኛዋ ትርሲት ነበረች ። ባሏንና ከልቧ የምትወዳቸዉን ሌሎቹን ጓዶቿን በግፍ የገደለባትን ጨካኝ አገዛዝ በሙሉ ነፍሷ ትጠላዋለች ። ይሁን እንጂ ፈጽሞዉኑ በቂም-በቀል አስፈላጊነት የምታምን አልነበረችም ።ይልቁኑ እጅጉን ቅን ፤ የሌሎችን ችግር ለመረዳት የፈጠነ ደግኛ ተፈጥሮና ሰፊ አስተሳሰብ የተቸራት ሴት ነበረች ። በማናቸዉም የንድፈ ሃሳብና ፍልስፍና ቀመስ በሆኑ ውይይቶችና ክርክሮች ለመሳተፍ በሚያበቃት ደረጃ ራሷን በጥልቅ ንባብ አበልጽጋለች ። የዚያኑ ያህልም በዝቅተኛዉ የኑሮ እርከን ለሚማስኑት ወንድና ሴት አርሶአደሮች ሕይወት በጣሙን ቅርብ ነበረች ። በዚህም ሳቢያ በቀላሉ እንዲረዷትና እንዲያፈቅሯት አስችሏታል ። ምንጊዜም ፈጥኖ ደራሻቸዉ የነበረች በመሆኗ የተነሳ ተዋጊዎቹም ጭምር ከልብ ይወድዷት ነበር ።

ትርሲት እንደቅርብ ጓዶቿ ሁሉ ፤ ከትግሉ ጋር ተያይዘዉ የገጠሟትን ችግሮችና ዕልህ አስጨራሽ ዉጣ ዉረዶችን ሁላ ተቋቁማ አልፋቻዋለች ።የዚህ ሁሉ ጽናቷ መሠረቱ ለዓላማዋና ለሕዝብ የነበራት ጥብቅ እምነትና ፍቅር ብቻ አልነበረም ፤ ለዛ ላለዉ ጨዋታና ሳቅ የነበራት ችሎታ ጭምር እንጂ ። በየዕለቱ የሚያጋጥሙትን ችግሮች ሁሉ ስቆ ማሳለፍን ከተካኑት መሃከል አንዷ ነበረች ። ስለ ማንኛዉም ጉዳይ ከሚገባዉ በላይ በማሰብ ጊዜዋን የምታባክን አይነት አልነበረችም ። የአሜሪካዊዉን ጸሀፊና ኮሜዲያን -የዊልያም ፊልድስን አባባል አዘዉትራ በመጥቀስ ፤ ራሷን “በየደቂቃዉ ከሚወለዱት ጅላንፎዎች” አንዷ እንደሆነች አድርጋ መቁጠር ይቀናት ነበር ። ይህም ሆኖ ፤ ትርሲት በጣሙን ጠንካራና አይወላዉሌ ሴት ነበረች ። በጥብቅ ሥነ ስርዓት የታነጸች ፤ ከመርህ ዉልፍት የማትል ኮስታራም ነች ።

የአንድ መቶ ሰባ ሁለቱን (፻፸፪ )ገጽ ጽሑፏን ያሰፈረችዉ በእንግሊዝኛ ነበር ። በጻፈችልኝ ማስታወሻ ዉስጥ “እንግሊዝኛዬ ዝጓልና ዐርመዉ ፤” ብላኝ የነበረ ቢሆንም ዕርማት አስፈላጊ ሆኖ ስላላገኘሁት እንዳለችኝ አላደረግኩም ። የኋላ ኋላ ጥርት ያለ “የባላገር አማርኛ” ስትናገር የነበረዉን ያህል ስትናገርም ሆነ ስትጽፍ እንግሊዝኛዋ ግሩም ነበር ። ትርሲት ሁሌም ከማጥናትና ይበልጥ ለማወቅ ከመጣር ቦዝና አታዉቅም ። ታሪኳን ለመግለጽ የተጠቀመችበት የአተራረክ ስልት በራሱ የተላበሰችዉን ፤ ዕዉቀትን አልጠግብ ባይ ስሱ ሰብዕናዋን አግዝፎ ያሳየናል ። ዕዉነቱን ለመናገር፤ ርሷን ለመሰለች ወጣት ጓድ ለመሆን መብቃት በራሱ መታደልም ፤ ክብርም ጭምር ነዉ ።

ትርሲት ተከሉ እና
ገነት ግርማ (በቋራ)



ትርሲት ከአዲስ አበባዉ ቀይ ሽብር በህይወት ተርፋለች ። ድርጅቷ ኢሕአፓ በገጠር ያደረጋቸዉን አያሌ ዉጊያዎችና ያጋጠሙትን ችግሮችም በሙሉ ተቁቁማ አልፋቸዋለች ። ይሁን እንጂ ፤ በጥቂት ሤረኞች የሚመራዉና ራሱን ሕወሀት ብሎ የሚጠራዉ ኋላ ቀር የዘረኞች ቡድን ከአገዛዙ የሥልጣን ማማ ላይ ፊጥ ማለቱን በቁጭት ከማየቷ በፊት ፤ በልብ ሕመም ሳቢያ በሞት ተለይታለች ። ጸጋዬ ገብረ መድህንን ፤ ይስሃቅ ደብረጽዮንን፤ ስጦታዉ ሑሴንን ፤ በለጠ አምሐን ፤ ጥቂት ቆይቶም አበራሽ በርታን የመሳሰሉ የቅርብ ጓዶቿ ከትግራይ ከፈለቁት ነፍሰ ገዳይ ወሮ በላዎች እጅ ሲወድቁ በቁም መመልከቱ ከሚያስከትለዉ የልብ ስብራት ማገገም አትችልም ነበርና ተፈጥሮአዊዉ ሞቷ ከግልግል ሊቆጠር ይበቃ ይሆናል ። ይህ ግምት ግን ዛሬም በአጸደ ሥጋ ከመሀከላችን ሁና፤ ከአካላዊና አዕምሮአዊ ጥንካሬዋ ፤ ከደፋርነቷና ከታላቁ የመሥዋዕት መንፈሷ ጸጋ ቢሰርጽልን የምንመርጥ መሆኑን ከቶ አያደበዝዘዉም ።

ዙሪያ ገባችንን ስንቃኝ ፤ ያሳለፍነዉ አሳዛኝ ትርዒት ዛሬም ተመልሶ ሲደገም እናስተዉላለን ። ደርግ ሞቶ ተቀብሯል ። ይሁን እንጂ ሕወሀት ለትንሳዔዉ አብቅቶታል ። ጠመንጃ ሕግ የሆነበት ፤ መንግሥታዊ ሽብር አሁንም እንደቀጠለ ነዉ ። ለሽብሩ ስም አይዉጣለት ፤ የተለየ ቀለም አይሰጠዉ እንጂ መኖሩ ርግጠኛ ነዉ ፤ ሰለባዎቹ ተከታትለዉ ሲወድቁ እያየን ነዉ ። ላመኑበት ዓላማ ሲሉ የመጣዉን መከራና የተጠየቁትን መሥዋዕት በትዕግስት ለሚቀበሉ ፤ለሀገራቸዉና ለወገኖቻቸዉ ባላቸዉ ፍቅር ለሚነድዱ ትርሲትን ለመሳሰሉ የሕዝብ ልጆች ሁሉ የሚደረገዉ ጥሪ ግልጽና ጎልቶ የሚሰማ ነዉ ። መንግሥቱንና ቀልቤሣን በመሳሰሉ ጭራቆች እግር ቀንደኛዎቹ የወያኔ ወንጀለኞች ተተክተዋል ፤ በመሆኑም ኢትዮጵያ ትርሲትን የመሰሉ ሴቶችና ብርቅዬዎቹን ጓዶቿን የመሳሰሉ ወንዶች ልጆቿን አበክራ ትሻለች ።

በዚህ ጽሁፍ የሠፈረዉ የትርሲት ታሪክ ቅንጭብ ነዉ ። ሆኖም በታሪኳ ላይም ሆነ ፤ ለትግሉ ቤዛ በሆነዉ ሕይወቷ ዙሪያ የጠለቀ ምርምር ለማድረግ ፍላጎቱ ላላቸዉ ወገኖች የሚያግዝ ተጨማሪ ዋቤ ጽሁፍ መኖሩን መጠቆሙ አግባብነት አያጣም ። **( ከፊሉ የትርሲት ታሪክ ፤ ከተሳታፊዎቹ መሃከል የጥቂቶቹ ስም ለደኅንነታቸዉ ሲባል ተለዉጦ ፤ ባቢሌ ቶላ በአዉሮፓዉያኑ የዘመን ቀመር ፩፱፻፺፱ ላይ፤ “ቱ ኪል ኤ ጄኔሬሽን ፤ ዘ ሬድ ቴሬር ኢን ኢትዮጵያ ፤” በሚል ርዕስ ባሳተሙት መጽሐፍ ዉስጥ ተካትቷል ።)**

**ይቀጥላል........**

**ባለፉት ተከታታይ ዕትሞች ፤ በዚህ ዐምድ ሥር ሲነበብ የከረመዉን ደማቁን የነጌሌ ቦረና የኢሕአፓ ወጣት ሊግ (ኢሕአወሊ) አባላት ገድል እነሆ ደመደምን ። እኛ በጽሑፍ እናስፍረዉ እንጂ ፤በዚያ ወርቃማ ትዉልድ የቆየልን አገርንና ወገንን የማፍቀር እጹብ ድንቅ የተጋድሎ ታሪክ በደምና በህይወት መሥዋዕት ደማቅ ቀለም ነዉ የታተመዉ ። ተወደደም ተጠላም ከትዉልድ ወደ ትዉልድ እየተወራረሰ ፤ ከከሃዲዎች ሁሉ ጋር በኅሊና ሸንጎ ተሟግቶ እየረታ የሚበረታ ፤ የጠራ ኢትዮጵያዊ የእዉነት መስመር ስለመሆኑ ጥርጥር የለዉም ። በዚሁ ዓላማ ጠገግ ፤ በቀጣይ ባለተራነት ፤ አገራቸዉንና ወገናቸዉን ያሉ የታላቁ የኢትዮጵያ ህዝብ ሴት ልጆች በፍቅር፤ በዉበት፤ በጠነከረ እምነትና ወኔ አስጊጠዉ ካስቀሩልን አያሌ ሕዝባዊና አብዮታዊ የተጋድሎ ታሪኮች ዉስጥ አንዱን ይዘን ቀርበናል ። ከትረካው ወጣኒነት እስከ መግቢያዉ ድረስ የድንቅ ብዕሩን ትሩፋት ላቋደሰን ደራሲ ለባቢሌ ቶላ ፤ እንዲሁም በጎደለበት ሁሉ ለሞላችሁልን የጓድ ቆንጂት ቤተሰቦች ሁሉ ምስጋናችን ይድረሳችሁ ።**

## በቀይ ሽብር የሞት ጥላ ሥር ፤
## የጓድ ቆንጂት ተክሉ ከራሞት

የታመነችለት ታላቅ ዓላማ የርሷን መኖር ይሻዉ እንደነበረዉ ሁሉ ፤ ትርሲትም በሕይወት ኖራ የበለጠ ለመታገል ስትል ፤ ከቀዩ ሽብር ፋሺስታዊ ፍጅት ለመትረፍ ቆርጣ መነሳቷን ከጽሑፏ እንረዳለን ። በሥራ የተረጎመችዉም ይህንኑ ነበር ፦ በቃል ሳይሆን - በግብር ፤ ከሩቁ ሳይሆን - እዚያዉ ድረስ ሄዳ ከሕዝቡ ጎን በመቆም ፤ ለድለላ ሳይሆን - ችግር ጉስቁልናቸዉን አብራ እየኖረች በመካፈልና ሞታቸዉን ፊት ለፊት በመጋፈጥ ፤ በጀግንነት ኖራ በጀግንነት አርፋለች ። በበኩሌ ፤ ትርሲትን ለማወቅ በመቻሌ ክብር ይሰማኛል ። (ባቢሌ ቶላ)

### ፩

የትም ሆነ የት ፤ አንገቱን ዘወር አድርጎ ለተመለከተ ሁሉ ፤ ብረት ለበስ መኪናዎች - በየዐይነታቸዉ ከዐይን ይገባሉ ። ሬንጅ ሮቨሮች ፤.... ጂፖች ፤ .....ሸፍን ቮልስ ዋገኖች ፤ ... ወዘተ ......በዝግተኛ ፍጥነት ጎዳናዎችን ያካልላሉ ። እያንዳንዱ ተሽከርካሪ እስካፍንጫቸዉ የታጠቁ ወታደሮችንና የደህንነት አባላትን አጭቆ ጭኗል ። የሲቪል ልብስ የለበሱቱ ፤ ከጨርቅ የተሰፉ ባርኔጣዎችን ከመድፋታቸዉም በላይ ዘናጭ ጥቋቁር መነጽሮች አድርገዉ የጃኬቶቻቸዉን ኮሌታዎች ወደ ላይ ቀስረዋቸዋል ። ይህም ፍጹም ተራ ዱርዬ ወይም በመናኛ ሲኒማ ዉስጥ የሚገኝ ገጸ-ባህሪ አስመስሏቸዋል ። የኮማንዶ ሬንጀር የደንብ ልብስ የለበሱ ወታደሮች ዕይታ በራሱ በፍርሃት ያንዘፈዝፋል ። በጂፖቹ ላይ የተጠመዱባቸዉን ቢ አር መትረየሶች ፤ እንዲሁም በተሽከርካሪዎቹ ክፍት መስኮቶች ወደ ዉጭ የተወደሩትን፤ የደህንነት ታጣቂዎቹ የታጠቋቸዉን የኤኬ47 (ክላሺንኮቭ) እና የተለያየ ስሪት ያላቸዉን ጠብመንጃዎች አፈሙዞች በቅርብ ሆኖ መመልከት መላ አካላትን የሽብር ብርክ ያስይዛል ።

ታጣቂዎቹ ተሳፋሪዎች ፤ በየጎዳናዉና በየመሿለኪያዉ የሚተላለፈዉን እያንዳንዱን ሰዉ በአሻጋሪ ሆነዉ በጥንቃቄ ለመመልከት እንዲችሉ ተብሎ ፤ ተሽከርካሪዎቹ ከልጅ ሩጫ ባልተሻለ ፍጥነት ነበር የሚጓዙት። ደርግ ለሚቆጣጠረዉ የሠራተኞች ማህበር (መኢሠማ) ሊቀ መንበር የነበረዉን ተመስገን ማዴቦን ለመዘከር ፤ እነዚያን ጥልማሞት መኪኖች " የማዴቦ ፈረሶች፤'' እያልን ነበር የምንጠራቸዉ ። ማርቆስ ሀጎስን የመሳሰሉ ሀቀኛ መሪዎቹ በአገዛዙ ከተገደሉ በኋላ እንዲፈርስ በተደረገዉ አይበገሬ የኢትዮጵያ የሠራተኛ ማህበራት ኮንፌዴሬሽን (ኢሠማኮ ) ምትክ ለተቋቋመዉ መኢሠማ በሊቀ መንበርነት የተሰየመዉ ተመስገን ማዴቦ ፤ በመዲናይቱ አዉራ ጎዳናዎች ላይ የሚካሄዱትን "አስሶ የመደምሰስ" ተልዕኮዎችም በግንባር ቀደምነት ከሚያስፈጽሙት ዐረመኔ ፋሺስቶች አንዱ ነበር ። ያለ አንዳች ተጠያቂነት እንዳሰኛቸዉ ለመግደል ወይም ለማሰር ልዩ ፈቃድ የተሰጣቸዉ በደም ጥም የናወዙ ነፍሰ ገዳዮች፤ በይፋ የተሰማሩባቸዉን ግድያን ፤ ስየልንና እስራትን የሚያካትቱትን የ "ነጻ ርምጃ" ተከታታይ ዘመቻዎች ካስጀመሩት ሰዎችም አንዱ ተመስገን ነዉ።

ተመስገን ማዴቦ ፤ ዘወትር አመሻሽ ላይ ብረት ለበሱን አጀቡን አስከትሎ በመኢሠማ ዋና ጽ/ቤት አቅራቢያ የሚገኙትን አዉራ መንገዶች የማካለል ልማድ ነበረዉ ።እዚያም ፤ ኤኬ-አርባ ሰባት (ካላሺን) ጠመንጃዉን አንግቶና ሁሌም ተፈጥሮአዊ ክፋቱን ከማይደብቅ የፊቱ ገጽ ላይ ዕብሪቱን አጉልቶ እያስነበበ ፤ ያጋጠመዉን ሁሉ እያስቆመ ይፈትሻል ፤ በምርመራ ጥያቄ ያዋክባል ፤ ይረሽናልም ። ድንገተኛ ሞት በተለመደበት በዚያ ዘመን ፤ በማዴቦ የግድያ ቡድን ከተደበደቡ በኋላ በነጻ ለመለቀቅ መቻል ከመታደል እኩል ነበር የሚቆጠረዉ ።

# ትናንትና

በ፲፱፻፷፱ ዓ.ም ኅዳር ዉስጥ ደንገዝገዝ ባለ አንድ ምሽት በጋንዲ መታሰቢያ ሆስፒታል አጠገብ ከሚገኝ ጎዳና ላይ ፤ ነፍሰ ገዳዮቹ ቡድኖች " የአናርኪስቶች አለባበስ " ብለዉ በሚጠሩት አኳኋን ተላብሰን በመዘጋጀት ወጥመዳችንን አጠመድን ። የሚያድነዉን ወገን ከሩቁ የተመለከተዉ የማዴቦ ገዳይ ቡድንም በፍጥነት መኪናዉን አቆመ ። ወዲያዉኑም ተመስገን ማዴቦና ሁለት አጃቢዎቹ ታዳኙ ወደሚገኝበት ሥፍራ ዘልለዉ ለመዉረድ የመኪናቸዉን በሮች ከፈቱ ። በዚህ ጊዜም አንድ ሁለት ዑዚ ጠመንጃዎችንና አንድ የእጅ ቦምብ ታጥቀ የወጣዉ የመከላከያ አሀዳችን ፤ ተመስገን ማዴቦንና አጃቢዎቹን ከመደምሰሱም በላይ አንድ የተበላሸ ካላሺንኮቭ ጠመንጃ ማርኳል ። በምርኮ የተገኘዉ ያ ጠመንጃ ጥገና ተደርጎለት ቀጥለዉ በተከናወኑ ግዳጆች ላይ አገልግሎት ሰጥቷል ። የመከላከያ አሀዳችን ግዳጁን ከፈጸመ በኋላ ፤ ጥቂት ፈንጠር ብሎ የመከላከያ ሚኒስቴርን ከብቦ ከሚጠብቀዉ የብረት ለበስ ዘብ አፍንጫ ሥር በአስደናቂ ፍጥነት አምልጦ በመዉጣት በተሳካ ሁኔታ ሊሰወር ችሏል ።

ታማኝ ሎሌዉን ያጣዉ የደርግ አገዛዝ ፤ በ "አብዮት አደባባይ" ፤ ቀጥሎም " በተለይ ለአብዮታዉያን " በመደበዉ የመቃብር ሥፍራ ፤ ከዚያ ቀደም የተከናወኑትን ሁሉ የሚያስንቅ ደማቅ የቀብር ስነ ሥርዓት አከናወነ ። በየስነ ሥርዓቱም ላይ እንደተለመደዉ ፤ በመከላከያ አሀዶቻችን በሚገደል በእያንዳንዱ " አብዮታዊ " ምትክ ሺህ " ሥርዓተ አልበኞችን " ለመግደል የገቡትን ቃል ኪዳናቸዉን አድሰዉታል ። ልክ የጀርመን ናዚዎች የተነሳባቸዉን ሕዝባዊ ተቃዉሞ ለመጨፍለቅ ከወሰዷቸዉ የጅምላ ግድያዎችና የኃይል ርምጃዎች ጋር የሚመሳሰል ተግባር ነበር ። ሕዝባችን እንደሚያዉቀዉ ፤ በእኛ በኩል ራሳችንን ከጥቃት ለመከላከል ለወሰድናቸዉ ርምጃዎች በሙሉ መንስዔዉ የአገዛዙ የማያባራ እመቃና ገደብ የለሽ ግድያ ነበር ። የደርጉ አገዛዝ የመጀመሪያዉን ጥይት የተኮሰ ከመሆኑም በላይ በፖለቲካዉ መስክ በምናደርገዉ ትግል እያቸነፍነዉ መሆኑ ግልጽ እየሆነ እንደመጣ ፤ " ሥርዓተ አልበኞችን ለመደምሰስ " የጭፍጨፋ ዉሳኔዉን አሳልፏል ።

ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተጠናከረ የሚሄደዉ መንግሥታዊ እመቃና ሽብር ከጅምሩ ከወታደራዊዉ አገዛዝ ተፈጥሮ ጋር በጽኑዉ የተሰናሰለ ባህሪ ቢሆንም በስፋትና በተጧጧፈ መልክ መካሄድ የጀመረዉ አዲሱ የእመቃ ዘመቻ በከተማይቱ ዉስጥ በየትኛዉም ሥፍራ ጎልቶ የሚታይ ሊሆን በቅቷል ። " የማዴቦ ፈረሶች" ፤ ቁጥር በማይገልጠዉ መጠን ፤ ሞትን ለሁሉም አዳረሱ ። የግብር ይዉጣ ፤ ሥፍራ ሳይመርጡ የተሰቀሉትና በፈኩና ሥነ ልቦናዊ ተጽዕኖ በሚያሳድሩ ቀለሞች የተጻፉት መፈክሮችም ይህንኑ የሚለፍፉ ነበሩ ። .... " ቀዩን ሽብር እናፋፍማለን /".... " ዴሞን በዲሞትፎር ግደል /" .... ( ዴሞ ፤ የኢሕአፓ ልሳን ከሆነዉ " ዴሞክራሲያ " የተፈጠረ ምህጻረ ቃል ሲሆን አገዛዙ የኢሕአፓን አባላት በጥቅል የሚጠራበት ስያሜ ሊሆን በቅቷል ። )

ከየካቲት ፳፯ የካድሬዎች ማሰልጠኛ ት/ቤት ፤ከህዝብ ድርጅት ጉዳይ ጊዜያዊ ጽ/ቤትና ከአምስቱ " ህቡዕ " ማርክሳዊ ሌኒናዊ ድርጅቶች የተመራረጡ የርዕዮተ ዓለም አቀንቃኞቻቸዉ ፤ እስከ አፍንጫቸዉ ድረስ ታጥቀዉ ፤ በየከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቱ ፤ በየፋብሪካዉ ፤ በየመሥሪያ ቤቱና "የኢሕአፓ ምሽጎች" በየሚባሉት ሥፍራዎች ሁሉ ተሰራጩ ። .... { አምስቱ " ህቡዕ " ድርጅቶች ፤... ፩/ የመንግሥቱ ኃ/ማርያሙ አብዮታዊ ሰደድ ፤... ፪/ የኃይሌ ፊዳዉ መኢሶን .....፫/ የባሮ ቱምሳዉ ኢጭአት....፬/ የተስፋዬ መኮንኑ ማሌሪድ .... ፭/ የሠናይ ልኬው ወዝ ሊግ ናቸዉ ። } " ሥርዓተ አልበኞችን " የመመንጠር ዘመቻቸዉንም ተማሪዎችን ፤ ሠራተኞችን ፤ ወዘተ....... በስብሰባ አዳራሾች ዉስጥ ከሰበሰቡ በኋላ ተሰብሳቢዉን ሕዝብ በማስፈራራትና ሽብር በመንዛት ጀመሩት ። ማስፈራሪያዎቹና ጣጠኛዉ የ" አጋልጥ - ተጋለጥ " ክንዉኖችና በየጣልቃዉ የኢሕአፓን አቋሞችና መርህ በጽንሰ ሃሳብ ደረጃ ርባና ለማሳጣት ይቀርቡ የነበሩት ተራ መሟገቻዎች ከታቀደላቸዉ ዉጤት በተቃራኒዉ ፤ የአገዛዙን ካድሬዎች ርዕዮተ ዓለማዊ ድኅነትና ግራ የተጋባ አቋም የሚያጋልጡ ነበሩ ። ዋና የማሳመኛ ዘዴአቸዉም ቢሆን ያዉ ሽብር እንጂ ሌላ አልነበረም ። እያንዳንዱን ተጠርጣሪ "ሥርዓተ አልበኛ" እያዳፉ ከስብሰባዉ አዳራሽ ካስወጡት በኋላ አካላዊ እንግልትና ድብደባ ይፈጸምበታል ፤ በርሸናም ያስፈራሩታል ። አዳራሹ ዉስጥ ለቀሩት ደግሞ ወደ አብዮቱ ሠፈር ካልተቀላቀሉ በቀር ተመሳሳይ ስቃይ እንደሚጠብቃቸዉና ቀይ ሽብር እንደሚፋፋምባቸዉ ይነግሯቸዋል ።

ጥቂት ቆይተዉ ፤ በከተማ ነዋሪዎች ማህበራት (ቀበሌዎችና ከፍተኛዎች ) ፤በፋብሪካዎች ፤በተጎራባች የገበሬ ማህበራትና በሌሎች ተቋማት ሥር የሚገኙ "አብዮት ጠባቂዎች" ሳይቀሩ ጡንቻቸዉን ማሳዬት ጀመሩ ። የፍሳሽ መዉረጃዎችንና ሸሸጉን የከተማይቱን ገጽ ተጠግተዉ የሚኖሩትን ወስላቶችና ቀንደኛ ቀንደኛ ወንጀለኞች መልምለዉ ፤ አሠልጥነዉና አስታጥቀዉ በስራቸዉ ካሰለፉ በኋላ በእኛ ላይ ያቀዷቸዉን የጥቃት ዘመቻዎች ከፈቱብን ። ዘወትር ማለዳ ላይ እነዚሁ ነፍሰ በላዎች ፤ ጸረ - ኢሕአፓ መፈክሮችን በጩኸት እያሰሙና ለ"ሥርዓተ አልበኞች" ሞት የገቡትን ቃል - ኪዳን እያኧጎደጎዱ የሠልፍ ልምምድ ያደርጋሉ ። እነዚህ ልምምዶች በሕዝቡ ልብ ዉስጥ ፍርሀትን ለማስረጽ ታቅደዉ የሚከናወኑ ናቸዉ ። ካድሬዎቹ ኤኬ አርባ ሰባት (ክላሺንኮቭ )ና ሌሎች ሙሉና ከፊል አዉቶማቲክ ጠመንጃዎችን የሚታጠቁ ሲሆን የአብዮት ጥበቃዉ ነብሰ- በላዎች ደግሞ እንደ ቺኮዝ ባሉ ባለቃታ መሣሪያዎች ይገለገላሉ ። ግድያን በሚመለከት ግን ሁሉም እኩል እንዳፈተታቸዉ ለመግደል የሚያስችል ፈቃድ ነበራቸዉ ።

**ይቀጥላል........**

ካለፈዉ የቀተለ

## በቀይ ሽብር የሞት ጥላ ሥር ፤ የጓድ ቆንጂት ተክሉ ክራሞት

## ፩

ገዳዮቹ " አብዮት ጥበቃዎች" ፤ ከእያንዳንዱ ቀበሌ ጋር በመዋቅር ተያይዘዉ በ"ቀይ ሽብር ግንባር" ስር ይሰለፋሉ ። የሁሉም የበላይ የ "ቀይ ሽብር ኮሚቴ" ሲሆን ተግባሮቻቸዉንና " ሥርዓተ አልበኞችን" በመመንጠር ረገድ የሚያሳዩትን የቁርጠኛነት ስሜት ይቆጣጠራል ። የቀይ ሽብር ኮሚቴ ፤ የደርግ አባል - ለገሰ አስፋዉን በመሳሰሉ ሰዉ በላ ፋሺስቶች የሚመራ ሲሆን አባላቱ ደግሞ በቀበሌዎችና በማህበራት መዋቅሮች ዉስጥ ሰርገዉ የገቡ ዴሞክራሲያዊ አቋም ያላቸዉን ወገኖች በማስወገድ ስልጣናቸዉን በቁጥጥር ስር እስከማዋል ድረስ ሙሉ ሥልጣን የተሰጣቸዉ ነበሩ ። ከሰይጣናዊ ፈቃዶቻቸዉና ግምኛ ግብሮቻቸዉ በመነጨም ፤ በጊዜዉ በከተማይቱ ዉስጥ ፍጹም የገለማና ለስሜት የሚሰቀጥጥ ድባብ ሰፍኖ ቆዬ ።

በታህሳስ ወር የመጀመሪያ ሳምንት አካባቢ በማዴቦ ከሚሰማሩት ተሽከርካሪዎች ሁለቱ ወደ መርካቶዉ የአንዋር መስጊድ ቅጽር ዘልቀዉ በመግባት ፴ (ሠላሳ ) የሚደርሱ ፤ ከከፋ ክ/ሀገር የመጡ ሙስሊም ተሳላሚዎችን ጨፍጭፈዉ ገደሉ ። ከጥቂት ቀናት በኋላ ፤ በአገዛዙ ቁጥጥር ስር የነበሩት መገናኛ ብዙሀን ጭፍጨፋዉን " የኃይማኖት ልዩነትን ተንተርሰዉ ጥፋት ለማቀጣጠል ያቀዱ ሥርዓተ አልበኞች" ድርጊት አድርገዉ ለማቅረብ ያልተሳካ ጥረት አደረጉ ።

በዚያን ሰሞን ፤ በመቶዎች የሚቆጠሩ ወጣቶች ፤ ሠራተኞች ፤ተማሪዎች ፤ መምሕራን ፤ ምሁራንና የመንግሥት ሠራተኞች ከየመኖሪያ ቤታቸዉና ከየሚሠሩበት ሥፍራ እየተለቀሙ የተያዙ ሲሆን ፤ ከዚያ በኋላም ዳግመኛ በአካል አልታዩም ። ተመልካቹን ሕዝብ ለማሸበር ሲባል ፤ ተጠርጣሪ "ሥርዓተ አልበኞች"ን በተጨናነቁ አካባቢዎች ፤ ሰዉ በብዛት የሚተረማመስበትን ሰዓት መርጦ መረሸን ሥራ ተደርጎ ተይዞ ነበር ። የፍጅት ግብራቸዉንም ፤ " አካሉ የተሸነታተፈ አንድ ሬሳ ያን ያህል ሰዉን ለማሸበርና በፍርሃት ለማስደንበር ከቻለ ..... ለምን በመቶዎች አናባዛዉም ???...." በሚል የጨካኞች ፈሊጥ አስደግፈዉ የተሠማሩበት ይመስላል ። በታላቅ ዐረመኔያዊ ፍላጎት ተዉጠዉ ፤ ገላቸዉ የተከታተፈ አስከሬኖችን አነባብረዉ ጎዳናዎች ላይ ከመሩ ፤ በመገንጠያ መንገዶች ፤ በአደባባዮች ፤ በድልድዮች ላይ ለዕይታ ደረደሯቸዉ ። በዚህ መልኩ ፤ " ለጥ ሰጥ ብለህ ተገዛ ....አለበለዚያ ግን...."፤ የሚለዉ የፋሺስታዊዉ አገዛዝ ሞትን ያዘለ መልዕክት በቁም ወደአሉቱ ዜጎች በመተላለፍ ላይ ነበር ።

ቅጥረኞቹ ነፍሰ በላዎች ፤ ሬሣዎቹን ለሕዝብ ዕይታ ወደ አዉራ መንገዶች ከመወርወራቸዉ በፊት ይጫወቱባቸዉ ነበር ። አንዳንዶቹ አስከሬኖች ራሳቸዉ የተቆረጠ ፤ ከፊሎቹ እጆቻቸዉና እግሮቻቸዉ እየተጎነደሉ በግንባሮቻቸዉ ላይ በሚስማር የተመቱባቸዉ ነበሩ ። ጥቂቶቹ ደግሞ በደረቶቻቸዉ ላይ በሚስማር የተመታ " ጸረ - አብዮተኛ ነበርኩ" የሚል መፈክር እንዲነበብ ተደርገዋል ። የከተማ ነዋሪዎች ማኅበራት (ከነማ ) ተመራጭ የአመራር አባላት የነበሩ ጥንድ ባልና ሚስት ከተገደሉ በኋላ ፊታዉራሪ ኃብተ ጊዮርጊስ ድልድይ ላይ የተጣሉ ሲሆን ገዳዮቻቸዉ አንድ የዉስኪ ጠርሙስ ፤ ሦስት ብርጭቆዎችና የአፄ ኃይለ ሥላሴ የትዳር ጓደኛ የነበሩት የእቴጌ መነን የፎቶ ምስል እንዲዳበሷቸዉ አድርገዋል ።

የጥንዶቹ ሰለባዎች በድን ገላም ፤ በሀምራዊ ቀለም በተጻፈ አስበርጋጊ የቀይ ሽብር ፖስተር " አጊጧል" ። ከፒያሳዉ የአዉጉስታ ሸሚዝ መሸጫ መደብር መተላለፊያ ሠርጥ ላይ አንዲት ወጣት ሴትና አንድ ወጣት ወንድ በደረታቸዉ ወድቀዋል ። ደማቁ ቀይ ደማቸዉ ፤ ከአረንጓዴያማዉ ቢጫ ግድግዳ ላይ በርከት ብሎ ተረጭቶበታል ። የሥጋቸዉ ቅንጥብጣቢዎች ከደንጊያና ከስሚንቶ የተሠራዉን ስንጥቅጥቅ ግድግዳ መርገዉታል ። እጅግ ከቀረበ ርቀት ተኩሰዉ እንደገደሏቸዉ በግልጽ ይታያል ። በዚያዉ ግድግዳ ላይ ፤ ከደማቸዉ እየተጠቀሰ በጉልድፍ የእጅ ጽሁፍ የተጻፈ ለማመን የሚከብድ ወለፈንዲ ይነበባል።

## ትናንትና

... "ከነዚህ ሥርዓተ አልበኞች ለፈሰሰዉ ደም ተጠያቂዉ ዴሞ ነዉ /" የሚል ። ነፍሰ በላዎቹ የሚከተሉት አንዳች አስፈሪ ስነ አመክንዮ ኖሯቸዉ ኖሯል ። ..."ሰለባችን ሆነህ ከእጃችን ለመዉደቅህ ተጠያቂዉ የገዛ ራስህ ነህ ፤" የሚል። ከዋዛ የለሹ አመክንዮ የሚመዘዝ አንዳች ቀልድ ቢኖር፤ ድቅድቅ ጽልመትና ዳፍንት የጋረደዉ ከመሆን አያልፍም።

ፒያሳ እምብርት ላይ የተጣለዉ የአስከሬን ቁልል ፤ የሰዉ ሥጋ ክምርና የሰዉ ደም ኩሬ ማለቱ ይቀላል ፤በአብዮት ጥበቃዎች ለበርካታ ሰዓታት ሲጠበቅ ቆዬ ። የጥበቃቸዉ ምክንያቱ ፤ አስከሬኖቹ በገዛ ራሳቸዉ ከወደቁበት ተነስተዉ ይሠወራሉ ወይም ሌላዉ አንስቶ ይቀብራቸዋል ከሚል ፍርሃት የተነሳ እንዳልሆነ ግልጽ ነበር ። ይልቁኑ ተመልካቾችን ለመፈተን ፤- ማን እንዳዘነ ፤ የማንንስ ዐይኖች ዕንባ እንዳቋሩና ማን ከቁጥጥሩ ዉጭ ራሱን በሥርዓተ አልበኛነት ወይም በደጋፊነት እንዳጋለጠ ለመከታተል ሲባል የሚደረግ ነበር ። ያንን ሲያደርግ የተገኘ ሰዉ ደግሞ የእስራትና የእንግልት እጮኛ መሆን አይቀርለትም ። ሕዝቡ ግና አዩት ወይ አላዩት ደንታ አልነበረዉም ።አንድ ታዛቢ እንደተናገረዉ ፤ በመቶዎች የሚቆጠሩ ሰዎች ያለቅሱ የነበረ ሲሆን የተቀሩት ደግሞ ቁጣና ንዴታቸዉን ይገልጹ ነበር ። ከዚያ የከፋ ሁኔታ ሊኖር እንደማይችል በሚገባ አዉቀዉታል ። እኔዉ ራሴ በዕንባ በተጋረዱ ዐይኖቼ ፤ ወደ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን በማምራት ላይ የነበሩ አንዲት ዕድሜያቸዉ የገፋ መነኩሲት ፤ ማን ምን ይለኛል ሳይሉ ፤ በዋይታ ደረታቸዉን እየመቱ ሙሾ ሲያወርዱ አይቻለሁ ። በዚያ የተጨናነቀ ጎዳና ላይ አዉቶቡስ ሲሳፈሩና ሲወርዱ የነበሩትም ፊታቸዉን በሃዘን ቅጭም ያደረጉ ሲሆን ከፊሎቹም አድራጎታቸዉ የሚያስከትለዉን ባለመፍራት ያለቅሱ ነበር ።

ከላይ የጠቀስኩትን የመሳሰሉ በመቶዎች የሚቆጠሩ ድርጊቶች በየዕለቱ ይፈጸሙ ነበር ። ሕዝቡ በድርጊቶቹ በርግጓልም ፤ ተቆጥቶማል ። በተቻለዉ አቅምም ለመቋቋም ሞክሯል ። ይህ ደግሞ በርግጥ እጅጉን ጠቃሚ የሆነ ሁነት ነበር ። እናም ከማኅበረሰቡ የተለያዩ ክፍሎች የፈለቁ ወጣቶችና አረጋዉያን የራስ አገዝ የመከላከያ ኮሚቴዎችን ለማቋቋም ተጣመሩ ። በኮልፌ ፤በተክለ ኃይማኖት ፤ በጎፋ ሠፈር ፤ በጎላ ሚካኤል ፤ በጣሊያን ሠፈርና በሌሎቹም አካባቢዎች የተዋቀሩት " የኡኡታ ኮሚቴዎች"፤ " የምከታ እና የ ፀረ- ዐፈና ኮሚቴዎች" በምሳሌነት የሚጠቀሱ ናቸዉ ። በዚህ ሁኔታ የተደራጁት የየአካባቢዉ ነዋሪዎች፤ የአገዛዙን የሌሊት አሳሾች ለማገድና ዐረመኔዎቹ ነፍሰ ገዳዮች የሚጓጓዙባቸውን ተሽከርካሪዎች ለመግታት የሚያስችሉ መሠናክሎችን ከማዘጋጀታቸዉም በላይ የመንገድ ዳር መብራቶችን አምፑሎች ይሰብሩ ነበር ። በድቅድቅ ጨለማ የሚደረጉት የሴቶች ኡኡታና ዋይታ ፤ እንዲሁም መጥበሻዎችንና መቀቀያ የብረት ድስቶችን በመምታት የሚፈጠሩት ድምጾች ነፍሰ ገዳዮቹን ከማስደንበራቸዉም በላይ ለተፈላጊዎቹ ሰለባዎች የማንቂያና የማስጠንቀቂያ ደወል ሆነዉ አገልግለዋል ። አንድ ምሽት ላይ ጎፋ ሠፈር ዉስጥ በተለመደዉ ተግባራቸዉ ላይ ተሰማርተዉ የነበሩ የአገዛዙ ነፍሰ ገዳዮች ፤ የአካባቢዉ የመከላከያ ኮሚቴዎች የወሰዷቸዉ መሰል ርምጃዎች ካሳደሩባቸዉ የጸና ፍርሐት የተነሳ ፤ የድጋፍ ጥሪ ያደረጉ ሲሆን ባለአዳኝ መብራት ሔሊኮፕተሮችና አነስተኛ ታንኮች በተደራቢነት ተሰልፈዉላቸዋል ።

በዚያዉ ዓመት የገና በዓል እየተቃረበ መምጣቱን ተከትሎ አሠሳው ፤ እገታዉና ፤ በአጠቃላይ ቀዩ ሽብር እየተጠናከረ ሄደ ። እግረኞችንና በመኪና ተጓጓዦችን ለመፈተሽ ሲባል እያንዳንዱን ጎዳና በደኅንነት ሠራተኞች ከሚገባዉ በላይ ማጨናነቅ የተለምዶ ሆነ ። ከአሠሳዎቹ የድግግሞሽ መጠን ፤ እንዲሁም ከሚታገቱት ፤ ከሚፈተሹትና በቁጥጥር ሥር ከሚዉሉት ሰዎች ቁጥር በመነሳት ወታደራዊዉ መስተዳድር ከጠቅላላዉ ህዝብ ዘጠና በመቶዉ " ሥርዓተ አልበኛ" (ኢሕአፓ) ሆኗል ብሎ ያምናል ከሚል ድምዳሜ መድረስ ይቻላል ። ቀበሌዎችና ከፍተኛዎች አዳዲስና ይበልጥ የተራቀቁ ጠመንጃዎች እንዲታጠቁ ተደርገዋል። ከ ኢ.አ 9501 እስከ ኢ.አ 9525 ባሉት ቁጥሮች የሚጀምሩ መንግሥታዊ ሰሌዳዎችን (ታርጋዎች) የለጠፉና ቢጫ ቀለም የተቀቡ ቮልስዋገን ሽፍን የማመላለሻ መኪኖች ለእያንዳንዱ ከፍተኛ ታድለዋል ።

ጃንሜዳ በሚገኘዉ የስፖርት ማዘዉተርያ ሥፍራ ተከታታይ የሥልጠና ልምምዶች በመደረግ ላይ ናቸዉ ። ከእያንዳንዱ ቀበሌና ከተለያዩ ተቋማት በጥንቃቄ ተመርጠዉ በድጋፍ ደብዳቤ ከተላኩ ከስምንት እስከ አስር በሚደርሱ የጥበቃ አባላት ተዉጣጥጥቶ የተደራጀዉና በታማኝነቱ ሌሎቹን የሚያስንቀዉ የአብዮት ጥበቃ ቡድንም ልዩና አፋጣኝ ኮርስ መከታተል ጀምሯል ። ይህ ለወደፊቱ በአስነዋሪ ግብሮቹ ስሙ የሚጠራ ግብረ ኃይል ልዩ ለሆነ ግዳጅ ብቃት እንዲኖረዉ በመሠልጠን ላይ ነበር ።

ይቀጥላል........

ካለፈዉ የቀተለ

# በቀይ ሽብር የሞት ጥላ ሥር ፤ የጓድ ቆንጂት ተክሉ ክራሞት

## ፩

የዚሁ ልዩ ኃይል ፤

ተልዕኮ ፤ "ከመርካቶ አካባቢ " ሥርዓተ አልበኞችን" መመንጠር ።

አካባቢያዊ ሁኔታ ፤ በ "ዴሞዎች" የተወረረ የጠላት ወረዳ ሲሆን ፤ ሙሉ ለሙሉ ለማለት በሚያስችል መጠን፤ ሕዝቡ በጠቅላላ የ "ሥርዓተ አልበኞቹ" ደጋፊ ነዉ ።

ስልት ፤ ድንገተኛነት ባለዉ ፍጥነት ዙሪያውን በመዝጋት መርካቶን ነጥሎ መቆጣጠር ።

የዕቅዱ መከወኛ ዘዴ ፤ ማንኛዉንም ሰዉ ፤ እያንዳንዱን ቤት ፤ እያንዳንዱን ኪዮስክ ፤ ሠዋራ ኪስ ቦታዎችንና ማዕዘናትን ሳይቀር መፈተሽና መበርበር ። ተቀባይነት ያለዉ መታወቂያ ያልያዘን ማንኛዉንም ሰዉ ማሰር ፤ አደገኛ ተጠርጣሪዎችን በኃይል መቆጣጠር ፤ ቀይ ሽብርን ማፋፋም ።

**ጊዜዉ ፤ በዐዉደ ዓመቱ ሰሞን ፤ ግብይቱ እጅግ በሚደራበት የገና ዋዜማ ዕለት፤ ሐሙስ - ከጠዋቱ አራት ሰዓት ተኩል ላይ ።**

**በዚያ የተረገመ ዕለት የሰለጠኑቱ አብዮት ጥበቃዎች ፤ ተሳፍረዉ ከመጡባቸዉ ማርቼዲስ የጭነት መኪኖች ላይ እየዘለሉ በመዉረድ በየምድብ ክፍሎቻቸዉ ቦታ ቦታቸዉን ያዙ ። ጠባቂዎቹ ቀደም ብለዉ ራሳቸዉን በቅኝት ፤ በፍተሻ ፤ በእስር ፤ በሽፋንና በድርጅት መምሪያ ቡድኖች ከፋፍለዉ መድበዋል ። ለግብረ ኃይሉ ድጋፍ እንዲሰጡ የተመደቡ ወታደሮችና ፖሊሶችም ምድብ ሥፍራዎቻቸዉን ያዙ ።**

የጥቃቱ ዒላማ የሆነዉ ጠላትስ ምን ይመስል ነበር ? ይህን በሚመለከት ፤ ጥቂት ምስለ ሃሳቦችን አቀርባለሁ ። መርካቶን በጥቂት ቃላት አጠቃልዬ ልስለዉ ብሞክር ፤ ማለት የምችለዉ እጅጉን የሚያደነጋግር ጉራንጉር መሆኑን ነው -- የአስፋልት ፤ የአፈር ጥርጊያ መንገድ ፤ ዉሽቅሽቅ ያሉ ቤቶች ጫካ ። ከሰዎች አንስቶ እስከ ቆሌዎቻቸዉና ሥምሪቶቻቸዉ ፤ ብሎም እስከ ሥነ ህንጻ ድረስ ሁሉ ነገር ድብልቅልቅ የሚሉበት ፤ ቅጣምባሩን ባጣ መልኩ ትዉፊታዊዉ ከዘመናዊዉ ፤ አሮጌዉ ከአዲሱ ጋር በአንድ የሚገማሸሩበት ሥፍራ ነዉ ። መርካቶ ሁለ ነገሩ በአያዎ (የማይመስል ግን እዉነት የሆነ ) የተመላ ነዉ። ከአንዲት በዉድ ልብሶች ከተሽቀረቀረች እመቤት ጎን ለጎን ያልጠገገና የሚያዥ ቁስል የወረሰዉን አካሉን ገሚስ ርቃን የተወ የሥጋ ደዌ በሽተኛ የሚታይበትን ያህል ፤ በአቧራማዉ ጎዳናዉ ላይ ሽንጠ ረዥሙ ማርቼዲስ ቤንዝ መኪና ከአቅም በላይ ተጭኖ ከሚያቃስት አህያ ጋር ይጋፋበታል ። የሚያስደንቀዉን ያህል ሊረዱት አዳጋች የሆነዉ መርካቶ ለተቃዋሚ ፖለቲከኞች ብቻ ሳይሆን ራሳቸዉን ከፖሊስ ለሚደብቁ ዜጎች ሁሉ መሰወሪያ ሆነዉ የሚያገለግሉ በርካታ ቤቶች ይገኙበታል ።

እርግጥ ነዉ ፤ የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ) በጠቅላላዉ ሕዝብ ልብና አዕምሮ ዉስጥ ዘልቋል ። ይሁን እንጂ ከድርጅቱ አንጻር መርካቶ ልዩና ሁነኛ ግምት የተሰጠዉ አካባቢ ነዉ ። መርካቶ ለእኛ ፤ አልጄሪያዉያን በጸረ ቅኝ አገዛዙ የትግል ዘመን "ካዝባህ " ብለዉ ለሚጠሩት ሥፍራ ይሰጡት የነበረዉን ያህል ልዩ ግምት ያላት ናት ። በመላዉ ዓለም ከሚገኘዉና አስከፊ በሆነ ጭቆናና ድህነት ከሚማቅቀዉ ሕዝብ ዉስጥ የተወሰነዉ ክፍል መርካቶ ዉስጥ ይኖራል ። ከዚህም በላይ መርካቶ የቱጃር ነጋዴዎች ፤ የመሃከለኛና የዝቅተኛ ቸርቻሪዎች ፤ የደላሎች ፤ የሊስትሮዎች ፤የሴትኛ አዳሪዎች ፤የቡና ቤትና የመሸታ ቤቶች ባለቤቶች ፤ የሠራተኞች ፤ የተማሪዎች ፤ የለማኞች ፤ ለአጭር ወይም ለረዢም ጊዜ ጉብኝት ወደ ሀገሪቱ መዲና የመጡ ገጠሬዎች ፤ የጡረተኛ ፖሊሶችና ወታደሮች ፤ በተለያየ ደረጃና አይነታ የሚገኙ ቁጭበሉዎች ፤ የስዉር ንግድ አካሃጆች ፤አነስተኛ ደመወዝ የሚከፈላቸዉ ሠራተኞች ፤ ወዘተ....ሁሉ መኖሪያ ናት ። ከነዚህ ዉስጥ አብዛኛዎቹ የኛዉ ዐይኖችና ጆሮዎች ሲሆኑ ለወታደራዊዉ አገዛዝ የነበረንን የከረረ ጥላቻም ይጋሩናል ።

ትንንሾቹ ሊስትሮዎች ቃፊሮቻችን የነበሩ ሲሆኑ መርካቶ ዉስጥ ከሚተረማመሰዉ የሰዉ መዓት ዉስጥ አንድን የደኅንነት አባል በቀላሉ ነጥሎ የማዉጣቱን ጥበብ ተክነዉበታል ። የቡና ቤት ባለቤቶች ፤ በተለይም የየምሽቱ ተረኛ ሴቶች ፤ ተዝቆ ለማያልቀዉ መረጃ ምንጮቻችን ነበሩ ። ከአፈር መደቦቻቸዉ ላይ ተቀምጠዉ አትክልት ፤በከፊል የተበላሹ ፍራፍሬዎች ፤ ቆሎና ቅመማ ቅመም የሚሸጡት የጉሊት ነጋዴ ሴቶችም ንቁ ደጋፊዎቻችን ናቸዉ ። እነዚህ የጉሊት ቸርቻሪዎች በቅርጫቶች ቁልል ተከብበዉ ፤ በመደዳ የቁጢጥ ከተቀመጡበት ሆነዉ ከፍ ባለ ድምጽ ሲንጫጩ ለተመለከተ በዙሪያ ገባቸዉ የሚከናወነዉን ድርጊያ የሚያስተዉሉ አይመስለዉም ። ለእኛ ግን ንቁ የመረጃ አቀባዮቻችን ነበሩ ። ካሉበት ሆነዉ የደኅንነት ሠራተኞችን ወይም ለተልዕኮ የተሰማራዉን አሳሽ ቡድን በቀላሉ ነጥለዉ ከለዩ በኋላ ብዙዉን ጊዜ እኛ -ታጋዮቹ የተለመደዉን "የቁም ስብሰባ" ወደምናደርግበት ጥጋት በጥድፊያ በመምጣት እንድንበተን ያስጠነቅቁናል ። በወቅቱ አብሮን መገኘት የሌለበትን መሳሪያ ወይም የሚበተን ወረቀት ይዘን ከሆነም በፍጥነት ተቀብለዉ ይደብቁልናል ። እዚያዉ በዚያዉ የሚያቀናብሯቸዉ የብልግና ስድድቦችና አካላዊ ምልክቶች የሚታከሉባቸዉ የጦፉ የጸብ ትዕይንቶች የአሳሹን ቡድን ትኩረት በማስለወጥ ወይም እንቅስቃሴዉን በማዘግዬት ያግዙናል ።

የእነዚህ ሴቶች ምልከታ እጅግ የሰላ መሆኑ ፤ የተለመደዉን " የዝንብ ጠንጋራ አዉቃለሁ ፤" የጉራ አባባል ለእዉነት ያቀርበዋል ። የአገዛዙን የደኅንነት ሠራተኞች ለይተዉ የሚያዉቋቸዉን ያህል እኛንም (ራሳችንን ለመለወጥ የምንጠቀምባቸዉ ዘዴዎች ሳያግዷቸዉ ) በቀላሉ ይለዩን ነበር ። በተቻለኝ አቅም አንዲት ምስኪን የቤት ሠራተኛ ተመስዬ በወጣሁባቸዉ ጊዜያት በአጠገባቸዉ ሳልፍ በስሜ ጠርተዉ አንድ ወይም ሁለት ሙዝ በነጻ ይሰጡኝና ሀዘኔታ በተጫነዉ ዐይን እያዩ "አይዞሽ፤" እያሉ ያበረታቱኛል ። ( ይታያችሁ ፤ በጊዜዉ ንግድ ፤ በስሙኒ ስድስት የገዙትን ሙዝ ቸርችረዉ ሰላሣ ሳንቲም ብቻ ነበር የሚያጣሩት ።)

# ትናንትና

ስለእነዚያ ሴቶች ማሰቡ በራሱ ህቡዕ ስለነበረዉ የሕይወቴ አንጓ እንድጽፍ በአንክሮ ይጎተጉተኛል ። ስለ ተመክሮዬ ስናገር ከሌሎች የተለየ ላይሆን እንደሚችል አበክሬ ማሳወቅ እወድዳለሁ ። በሺዎች የሚቆጠሩት ጓዶቻችን እጅጉን የገዘፈና የተለያየ የህቡዕ ትግል ተሞክሮ ያላቸዉ ናቸዉ ። በመሆኑም ከገዛ ራሴ ተመክሮ ብቻ በመነሳት በህቡዕ የተኖረዉ ሕይወት ይህንን ወይም ያንን ይመስላል ከሚል ማጠቃለያ ለመድረስ ያስቸግረኛል ። የኔዉ ታሪክ ፤ ብዙዎቹ ጓዶች ከኖሩት አንደኛዉና ተዳባይም የመሆኑን ያህል በራሱ ምልዐት ያለዉ ተሞክሮ ነዉ ።

## ፪

እንደ አንድ "ሕጋዊ" ሰዉ ሳደርጋቸዉ የነበሩትን እንቅስቃሴዎች በመግታት ራሴን ለመደበቅ የተገደድኩት በ፲፱፻፷፰ ዓ.ም አጋማሽ ላይ ነበር ። ባለትዳር ወጣቶች አስጠግተዉኝ የተጠለልኩባት ባለአንድ ክፍሏ ወሻቃ ቤት አዲስ አበባ ከተማ ዉስጥ ግንፍሌ አካባቢ ትገኛለች ። ቤቲቱ ፤ የባልና ሚስቱን መኝታ ፤ ተዳብሏቸዉ ይኖር የነበረ አንድ ሌላ ሰዉ ታጣፊ የመንገድ አልጋ ፤ እንዲሁም የምግብና የወጥ ቤት ዕቃዎች ማስቀመጫ የሆነዉን አንድ ጠረጴዛ አፋፍጋ ይዛለች ። ስንጥቅጥቅ የበዛባቸው የቤቱ የጭቃ ምርግ ግድግዳዎች በከፊል በሲኒማ ማስታወቂያ ወረቀቶች ተለጣጥፈዋል ። (ከእነዚሁም አንዱ "ቫላቿ ፔፐርስ" በሚል ርዕስ የሚታወቀዉ ፊልም ማስታወቂያ እንደነበር አስታዉሳለሁ ።) ቤቷ ለአራት ሰዎች የማትበቃ፤ በዉስጧም ርስበርስ ሳይገጫጩ ለመተላለፍ የማታስችል ነች ። የዕድል ሆኖ ግን በደባልነት የሚኖረዉ አራተኛዉ ሰዉዬ ሥራዉ በዋናዉ የንግድ ባንክ የሌት ዘበኛነት ነዉ ። የቤቱ አባ ወራ በአንድ የግል ት/ቤት የሚያስተምር በመሆኑ ቀን ቀን እቤት አይዉልም ። የቤት እመቤቲቱ ደግሞ የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ተማሪ ብትሆንም በወቅቱ የሠርክ በነበረዉ የተማሪዎች ረብሻና የትምህርት ማቆም አድማ ሳቢያ ት/ቤቷ በመዘጋቱ የተነሳ ቤት ነበር የምትዉለዉ ። በደባልነት ተጠግቶ የሚኖረዉን ሰዉ ግን እንኳን እኔ እዳባዮቹም አያዉቁትም ። ከአንድ ጣሪያ ሥር ለመኖር ያስገደዳቸዉ በጊዜዉ የነበረዉ ከፍተኛ የመኖሪያ ቤት እጥረት ነዉ ።

መኖሪያ ሠፈራችንም ራሱ ጭንቅንቅ ያለ ነዉ ። የኛ መኖሪያ ከሆነዉ ክፍል ጋር ከተያያዘዉ ሌላ ቤት ጋር አንድ ባለ አርባ ሻማ የኮረንቲ መብራት በጋራ እንጠቀማለን ። ለነገሩ እንጂ በዚያ ሠፈር ዉስጥ ከጎረቤቶቻችን ጋር የምንጋራዉ መገልገያ ኮረንቲዉ ብቻ አልነበረም ። በወል የምንቀዳዉ ቧምቧ ሁሌም ስለሚያፈስስ ፤ ዙሪያውን በቦካዉ ጭቃ ላይ ተረማምዶ ዉኃ ለማግኘት ከላስቲክ የተሠራ ቦት መጫማት ያስፈልግ ነበር ። ከጋራ አገልግሎት መስጫዎቻችን ሁሉ ዝነኛዉ በሠፈሩ ማዕከላዊ ሥፍራ ላይ የሚገኘዉ የመጸዳጃ ቤት ሲሆን ከመወጣጫ ደረጃዎቹ ግርጌ ከምር የሚያስቁ ትዕይንቶች በየዕለቱ ይከናወኑበታል ።

አንዳንዶቹ ፤ ለምንም ነገር ደንታ ሳይኖራቸዉ ገብተዉ ለሰዓታት ያህል ይወዘፉበታል ። ሌሎቹ ደግሞ ፤ በተለይም ሴቶቹ ፤ ወደ መጸዳጃዉ ቤት ሲገቡና ሲወጡ እንዲታዩ ፈጽሞ አይፈልጉም ። (ሴቶች ይህ ስነ-ሕይወታዊ ግዳጅ አይመለከታቸዉም በሚል ቅድመ እሳቤ የተነሳ ይሆንን ?? ) ፤ እናም ሴቶች ሽንት ለመክፈል ወደ መጸዳጃ ቤቱ የሚያመሩት በድብቅ ፤ በፊቶቻቸዉ ገጽታ ላይ ከፍተኛ ሀፍረት እየተነበበ ሲሆን ፤ ግራና ቀኝ ተገለማምጠዉ ማንም እንደማያያቸዉ ካጣሩ በኋላ እንደ ጥይት ተተኩሰዉ ይገባሉ። አንዳንዶች ደግሞ ከተፈጥሮአዊዉ ድርጊት ጋር የተቆራኙ አሳፋሪ ድምጾችን ለመሸፈን ሲሉ መጸዳጃ ቤት ዉስጥ ሆነዉ ይዘፍናሉ ወይም ያፏጫሉ ።

ለግምት ከሚያስቸግር በላይ እጅግ ከሚገማዉ ከዚያ የመጸዳጃ ቤት ዘልቀዉ ሲገቡ ፤ የኮምፔስታቶ ወለልና ከወለሉ አምስት ሳንቲ ሜትር ያህል ከፍ ባሉ አራት ቀጫጭን ጣዉላዎች ዙሪያዉን የተለበጠ የጉድጓዱ ጠባብ አፍ ፤ እንዲሁም ሰዎች የተጠቀሙባቸዉን የጽዳት ወረቀቶችና የጋዜጣ ቁርጥራጮችን የያዘዉ የቆሻሻ መጣያ ቅርጫት ይታያሉ ። ጉድጓዱ ላይ የተገጠመ አንዳችም መቀመጫ የሌለ በመሆኑ ተገልጋዩ ሰዉ የቁጢጥ በመቀመጥ ዐይነ ምድሩን አስተካክሎ ወደጉድጓዱ ማስገባት ይጠበቅበታል ። በዚያ ረገድ ፤ ከመጸዳጃ ቤቱ ተጠቃሚዎች ብዙዎቹ የተዋጣላቸዉ አልነበሩምና የነበረዉን ሁኔታ መገመቱ ላንባቢያኑ አይገድድም ። መጀመሪያ ላይ የቁጢጥ መቀመጡ ጡንቻ የሚሸመቅቅ ህመም እያስከተለብኝ ተቸግሬ የነበረ ቢሆንም ዉዬ አድሬ ልላመደዉ በቅቻለሁ ።

መላመድን የጠየቀኝ ሌላዉ ጉዳይ ምግብን ይመለከታል ። የምንመገበዉ ምግብ ሁልጊዜም የማያጠግብና ጣዕም የለሽ ነበር ። ሻይና ቡናማ ቀድሞ ነገር አይታሰቡም ። በወቅቱ ስኳር በቀበሌዎች አማካይነት የሚታደል ሲሆን ቡና ደግሞ በኪሎ ሃያ ብር ገብቷል ። ሁለት ሰዎችን ብቻ በያዘና በመምህር ደመወዝ በሚተዳደር ቤት ዉስጥ ከሚታየዉ የኑሮ ሁኔታ በመነሳት በላብ አደሮች ፤ በዘበኞችና በሌሎቹ ዝቅተኛ ገቢ በነበራቸዉ ቤተሰቦች መኖሪያ ሊኖር የሚችለዉን ሁኔታ መገመቱ ያን ያህል አላዳገተኝም ። አጋጣሚዉ በህይወቴ ለመጀመሪያ ጊዜ ከእዉነተኛዉ ረሃብ ጋር አስተዋዉቆኛል ። ከዚያ በፊት ከረሃብ ጋር የነበረኝ ዕዉቂያ ትርፍ የሰዉነቴን ክብደት ለመቀነስ ምግቤን በምቆጣጠርበት ጊዜ ብቻ የተከሰተ ነበር ። በዚህም ሳቢያ እርስ በራሱ የሚቃረን ስሜት አደረብኝ ። በአንድ በኩል ፤ አሳዛኝና አስቸጋሪ የሆነዉን ህይወት ለሚገፉትና ፤ በማይሟላ ፍላጎትና በእጦት መሃከል የዉጥር ለተያዙ ወገኖች ሁሉ ሀዘን ገባኝ ፤ ባዶነትም ተሰማኝ ። በሌላ በኩል ደግሞ ፤ ከልቤ ከማስብላቸዉና ክምጨነቅላቸዉ ዝቅተኛ የኅብረተሰቡ ክፍሎች የአኗኗር ዘይቤ ጋር ራሴን ለማዋሃድ ዕድል ባገኘሁበት በዚያ አጋጣሚ እጅግ ደስ ተሰኘሁ ።በጥቅሉ ፤ አጋጣሚዉን መፈተኛዬም ፤ የኑሮ ጉስቁልና በዕዉኑ ምን እንደሆነ እንድማርበትም የተሰጠኝ ልዩ ዕድል አድርጌ ነበር ያየሁት ።

ለሽፋን በተጠቀምኩበት በአዲሱ ማንነቴ ፤ ከባሌ ጋር ተፋትቼ ከምኖርባትና በወለጋ ጠቅላይ ግዛት ከምትገኝ ትንሽዬ ከተማ ወደ አዲስ አበባ የመጣሁ የመምህሩ አስጠጊዬ እህት ነኝ ። ከቤቱ እንድኖር ያስጠጋኝ ሰዉ በአጋጣሚ የሚናገረዉ አማርኛ ደግሞ በጣሙን የኦሮሚኛ የአነጋገር ስልት የተጫነዉ ሲሆን እኔ ግን በተቃራኒዉ ከፈለቅሁበት ማኅበረሰባዊ ዳራ የተነሳ ተመሳስዬ መገኘቱ አልሆነልኝም ። በጊዜዉ የተጠቀምኩበት አማርኛዬ ዳር አገር ከሚገኝ የገጠር ከተማ ከመጣች አንዲት አርሶ አደር ሴት ይልቅ ለአንድ የሰላም ጓድ አባል (አሜሪካዊ) አነጋገር ይበልጥ የሚቀርብ ነበር ። ሆኖም ግን ፤ ሲያድለኝ ያ የተጠጋሁበት ሰዉ ፤ አንድም - በፖለቲካዉ ረገድ ዐይኑን ገና ያልገለጠ ፤ አንድም ደግሞ - ደክሞት ከሥራዉ ወደቤቱ የሚገባ ነበርና ነገሮችን አገጣጥሞ ለመመልከትና በመስቀልኛ ጥያቄ ሊያጣድፈኝ የሚያስችለዉ በቂ ጊዜ አልነበረዉም ።

**ይቀጥላል........**

# ትናንትና

ካለፈዉ የቀተለ

## በቀይ ሽብር የሞት ጥላ ሥር ፤ የጓድ ቆንጂት ተክሉ ክራሞት

### ፪

ራሴን ለመደበቅ የተጠቀምኩበት ሽፋንም ፈጽሞዉኑ ተራ ነበር ። ሳደርገዉ የነበረዉ ቀለማማ ዐይነርግብ ከፊቴ ገጽ ላይ የራሱን አሻራ አሳርፎ ነበርና ለጸሀይ ተጋልጦ ይበልጥ ከጠቆረዉ የቆዳዬ ቀለምጋር ሲወዳደር ያለዉ ልዩነት በቀላሉ ይታያል ። ደበክበክ ብሎ ከወደ መቀመጫዬ ጠብሰቅ የሚል ሰዉነት ፤ እንዲሁም ቀይና ትንሽ ልጅ የሚያስመስል ፊት ነበረኝ ። የምለብሰዉ ጥለት የሌለዉ ተራ የሸማ ቀሚስ ቢሆንም አሳማኝ አለባበስ እንዳልነበረ ይታወቀኛል ። ጎረቤቶቻችንም ቢሆኑ ሲያናግሩኝ የማይባቸዉ ሁኔታም ሆነ የሚያሳዩኝ ፊት ፈጽሞ ቢጤያቸዉ አድርገዉ እንዳልተቀበሉኝ ያሳብቅባቸዉ ነበር ።

ከህቡዕ ቆይታዬ የመጀመርያዎቹን ሦስት ቀናት በባልና ሚስቱ አስጠጊዎቼ አልጋ ላይ የአልጋልብስ ተከናንቤ አሳለፍኩ ። ማስመሰያ ምክንያቴ ያዉ ከወለጋ እስከ አዲሳባ ያደረግኩት ረዥም ጉዞ ያደረሰብኝ የአካል ዝለት ነበር ። በአራተኛዉ ቀን ግን የድርጅታዊ ግንኙነቴን መስመር መልሼ ከዘረጋሁ በኋላ ወደ ደጅ ወጣሁ ። ፍጹም ግራ ከመጋባቴም በላይ የሁሉም ሰዉ ዐይን የሚመለከተኝ መስሎ ተሰማኝ ። በስጋት ተዉጬ በአራቱም ማዕዘናት ዙርያዬን አማትር ጀመር ። በርግጥም የሚከተሉኝ ጥቂት ዐይኖች አልታጡም ። እነዚያ ዐይኖች ግና የማንም ሳይሆኑ መናኛ ዕድል ሞካሪ- የቅንዝረኛ ሽማግሌዎች ዐይኖች ነበሩ ። ከወሎ ጠቅላይ ግዛት መምጣቴን የገመተ አንድ ሽማግሌ ፤ ራሱም የወሎ ሰዉ መሆኑን ከነገረኝ በኋላ በወርቅና በጌጣጌጥ ስጦታ ሊያባብለኝ ሙከራ አደረገ ። ከዚያም አልፎ ሊቆነጥጠኝ ሲሞክር ባለ በሌለ አቅሜ ስገፈትረዉ ያዩ ሰዎች ሳቁበት ፤ ተሳለቁበትም ። ይህን መሰሉን የወንዶች ጸባይና ድርጊት ብዙም ሳልቆይ የተላመድኩት ሲሆን በገሃዱ ህይወት ዉስጥ የሀገሬ ሴቶች የሚገኙበትን ተጨባጭ ሁኔታ ለማገናዘብ በቅቻለሁ። በራስ መተማመኔ እየሄደ በመጣ ጊዜም እኔዉ ራሴ ከቅንዝራሞቹና ከቢጤዎቻቸዉ ጋር ሆን ብዬ መላከፉን ገፋሁበት ። አልፎ አልፎ ጥሩ ሽፋን ሆኖ አገልግሎኛል ። በጨካኝ ወንድ ክህደት ሳቢያ ከተማ ዉስጥ ብቻዋን የምትሰቃየዉን ሴትና በመሰል ትርክቶች ዉስጥ የየዋሂቱን ግልገል ባህሪ ተላብሼ መጫወቱን ተካንኩበት ። ይህን በመሰሉ ጉዳዮች ዙርያ የሚያጠነጥን ወሬ ደግሞ በአዉቶቡስ ተራና በተመሳሳይ ሥፍራዎች ተመድበዉ የሚሰማሩትን የደኅንነት ሠራተኞች ጆሮ ለመሳብ የሚበቃ ጣዕም እንደማይኖረዉ ግልጽ ነበር ።

በጥቅሉ ሲታይ ፤ ምንም እንኳ አንዳንዴ ስቃይ ባያጣዉም ፤ ከአዲሱ ሁኔታ ጋር ራሴን ያዛመድኩበት የሽግግር ጊዜ ፈጥኖ ሊያልፍ ችሏል ። እንደቀድሞዬ በመኪና ሳይሆን፤ አዘዉትሬ በእግሬ መጓዝ ነበረብኝና ወፍራሞቹ ጭኖቼ ከሚያደርጉት የርስ በርስ ፍትጊያ የተነሳ የቆዳ ሽፍታ ወጣብኝ ። በንፍፊቶቼ ዕባጭ ህመም በጣም ተሰቃየሁ ። የሰዉነቴ ክብደት በጣም አጭር በሆነ ጊዜ ዉስጥ በብዙ ቀነሰ ።ይሁን እንጂ አቋራጭ መንገዶችን ና መሿለኪያዎችን ከማካለል አልተገታሁም። የአዲስ አበባን ትርኪምርኪ መኖሪያ ሠፈሮች ፤ በጫጫታ የተመሉትን የመሸታ ቤቶቿን ፤ የሻይ ቤቶቿንና የገበያ ሥፍራዎቿን አበጥሬ አወቅኳቸዉ ። ትምህርት ገበየሁ ። የምኖርባትን ከተማ ጠረን ፤ ሠዋራዎቹን ሥፍራዎቿን ፤ ጠመዝማዛ ጎዳናዎቿንና አቋራጭ መንገዶቿን ፤ በአጠቃላይም የዉሎ አዳሯን ምትና ድምጸት ለማወቅ በቃሁ ።

እያደር ፤ ራሴን ከሚተራመሰዉ የሰዉ አጀብ ተለይቼ የማልታወቅ - እንዲያዉም ፈጽሞ በዐይን ልታይ የማልችል አድርጌ ቆጠርኩት ። የቀድሞዉን መሥርያ ቤቴንና እኖርበት የነበረዉን አፓርተማ አልፌ በእግሬ እስከመጓዝ ደረስኩ ። በእያንዳንዱ ቀን ማለዳ በእግረኞቹ መተላለፊያ ላይ ፤ ከባህላዊዉ ሸማ ቀሚሶቻቸዉ ላይ የመሥሪያ ቤታቸዉን ስምና ዓርማ የተጠለፉባቸዉን ካፖርቶች የደረቡ ሠራተኞች የተቀየጡባቸዉ ሴቶች እጅብ ብለዉ እየተንጫጩ እምብዛም ገቢ ወደማያስገኝላቸዉ ሥራ ሲያመሩ መመልከት የተለመደ ነዉ ። ወደተለያዩ የቀጠሮ ሥፍራዎች ሳመራ አዘዉትሬ ራሴን ከነርሱ ጋር እቀይጥ ነበር ። አልፎ አልፎ ቢሮዬን ከሚያጸዱልኝ ሴቶች ኋላ ሆኜ በሄድኩባቸዉ አጋጣሚዎችም አንዳቸዉም እንኳ አላወቁኝም ።

ከነርሱም ሆነ ከዚያ ቀደም ከሚያዉቁኝ ሌሎች ሰዎች ጋር ፊትለፊት ሳልገጣጠም የቀረሁበት ጊዜ ሳይኖር ቀርቶ አልነበረም ። ሆኖም አንዳንዴ ዐይን ራሱ ከሚያየዉ ይልቅ ያላየዉን አምኖ የሚቀበልበት ጊዜ አለ ። ጓዶቼ እኔ ስለምገኝበት ሥፍራ ሆን ብለዉ ግራ የሚያጋቡ ወሬዎችን አሰራጭተዉ ነበርና ያዩኝ ሰዎች ዐይኖቻቸዉን ማመን አልቻሉም ። እርግጥ ነዉ ፤ ይህ አይነቱ ዘዴ ለተወሰነ ጊዜ ሠርቷል ።
ፈጽሞ ልላመደዉ ያልቻልኩት አንድ ነገር ቢኖር ገበያ ዉስጥ በዋጋ ተከራክሮ መገበያየቱን ነበር ። ይህ ሁኔታዬ በተቀሩት ሴቶች ( በቸርቻሪዎቹ ባለጉሊቶች ዘንድ ሳይቀር ) በጥርጣሬ እንድታይ ቢያደርገኝም ድርጊቴን ማስደገፊያ አዘዉትሬ በምላሽ የማቀርባቸዉ ጮርቃ ምክንያቶች ጥርጣሬዉን በማለዘብ ዐመኔታ ያስገኙልኝ ይመስላል ። በዚህ መልኩ የገዛኋቸዉን አትክልቶች የሞላሁበትን ቅርጫት አንግቤ ወዳሻኝ ሥፍራ መንቀሳቀስ ችያለሁ።

ከአትክልቶቹ ሥር ወይም አንዳንዴ በቅርጫቱ ዉስጥ ተያይዞ በተሠራ ልዩ መደበቂያ ዉስጥ በስዉር የሚበተኑ ወረቀቶች ፤ ወይም የተፈታታ ጠመንጃ ፤ ሽጉጦች ፤ፖስተሮች ፤የማባዣ ቀለሞች ፤ ጥይቶች ወይም በህቡዕ ለሚደረገዉ ትግል አስፈላጊ የሆነ ማናቸዉም ቁሳቁስ በስዉር ይጓጓዛል ። ቅርጫቱን በማልጠቀምበት ጊዜ የመቢያ ሳህኖችን ወይም የሚያብረቀርቁ ሽክላ ሰር የወተት ማለቢያዎችን የምገለገል ሲሆን በድብቅ የማጓጉዛቸዉን ነገሮች ከሥር በማድረግ ከላዩ እንጀራ አስቀምጥበታለሁ ። አንዳንዴም ከቋንቋ ዉጭ የተመሰጠሩ ( የኮድ) መልዕክቶች በዉስጣቸዉ የተጎሰጎሱባቸዉን ዳቦዎች ተሸክሜ እንቀሳቀስ ነበር ። የተለያዩ ቁሳቁሶችን የምናጓጉዝባቸዉ በርካታ ዘዴዎች ነበሩን ። በዚህ መልኩ በተለያዩ ሽፋኖች በመንቀሳቀስ የአገዛዙን አዉታሮች ከዕይታ ዉጭ ሆኖ የሚያመሰቃቅለዉ የህቡዕ ሠራዊት አካል ከሆኑት (ከተለያዩ የኅብረተሰቡ ክፍሎች ከተዉጣጡት በብዙ መቶዎች ከሚቆጠሩት ) ሴቶችና ወጣት ልጃገረዶች ጋር አብሬ ተሰልፌአለሁ ።

በአንደኛዉ ወር ቆይታዬ ፤ ህቡዕ በሆነዉ ህይወት ከጨቅላ ህጻንነት ተነስቼ ወደ ጉልምስና ልመነደግ በቃሁ ። በመጠለያነት ስገለገልበት የቆየሁበት ቤትም ከጊዜ ወደጊዜ የማያመቸኝ እየሆነ ሄደ ። በተለይም ጓዶቻችን በ፩፱፻፷፰ ዓ.ም መጋመሻ ላይ ( እ.ኤ. አ ፌብሯሪ 8 ፤1976 )መርካቶ ከሚገኝ አንድ የመንግሥት ባንክ ቅርንጫፍ አንድ ሚሊዮን ሦስት መቶ ሺህ ብር ለድርጅታችን ጥቅም እንዲዉል ካደረጉ በኋላ ፤ የፖለቲካ ብስለት ያልነበረዉ የቤቱ ደባል ለጥቅም የማጎብደድ ሃሳብ በአዕምሮዉ የሚመላለስ መሆኑ ይታይ ጀመር ። በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ዉስጥ ተቀጥሮ የሚሠራበትን የጥበቃ ሥራ እንዳያጣ በመስጋቱ "ርጉማኑን ሥርዓተ አልበኞች" መላልሶ ማዉገዝ አመጣ ። ሌላዉ ችግር የተጠለልኩበት ቤት ክፍሉ እጅግ ጠባብ ከመሆኑ የተነሳ ለመጻፍም ሆነ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ለሕትመት ሥራ የማያስችለኝ ነበር ። ተበታኝ ወረቀቶችንና ሌሎች ቁሳቁሶችን ለመደበቅም አስቸጋሪ ሆኖ አገኘሁት ። በተጨማሪም በድርጅታዊ ሥራ ከምገናኛቸዉ ሰዎች ጥቂቶቹ ወደቤት መምጣት መጀመራቸዉ ለጥርጣሬና ለቀበሌዎች ዐይን የሚያጋልጥ በመሆኑ የተነሳ ሌላ ቤት መቀየር የግድ ሆነብኝ።

አድራሻ ቀይሬ የገባሁበት አዲሱ ቤት ደግሞ እንደኔዉ ተደብቀዉ የሚኖሩ ሌሎች ሰዎችን ያዳበለ ነዉ ። ምንም እንኳ ስለማንነታችንም ሆነ ስለተሰማራንበት ተግባር ርስበርስ ገልጠን ያላወራን ቢሆንም ፤ ወዲያዉኑ የነርሱዉ ቢጤ መሆኔን ለመገመት አልተቸገሩም ። በዚህም ሳቢያ ይህኛዉንም ለቅቆ መሄድ ነበረብኝ ። ይህኛዉን ቤት ትቼ ከወጣሁ ከሦስት ቀናት በኋላ መጠጊያ ባደረግኩት አዲስ አካባቢ መኖር ጀመርኩ ።

በዚያ ከቶ በማይዘነጋ ቀን ድፍን አዲስ አበባ በተባራሪ ወሬ ይንቻቻ ነበር ። ያን ዘግናኝ ዕለት ፈጽሞ አልረሳዉም ። የሠራተኞች ማህበር( ኢሠማኮ ) ና የኢትዮጵያ ሴቶች አስተባባሪ ኮሚቴ ግንባር ቀደም ታጋይ የነበረችዉ ዳሮ ነጋሽ ፤አራት ኪሎ በሚገኘዉ የመኖሪያና የሥራ ቦታዋ በሆነዉ የብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት አጠገብ በግፍ ተገደለች ። ግድያዉን እጅግ ዘግናኝ ፤ የገዳዮቿን ወንጀልም እጅጉን የከፋ የጭካኔ ድርጊት የሚያደርገዉ ዳሮ በተገደለችበት ወቅት ወሯ የገባ ነፍሰ ጡር የነበረች መሆኑ ብቻ አልነበረም ። ገዳዮቿ ሆዷን ቀድደዉ ሽሉን የዘረገፉት ሲሆን አንድ የዐይን እማኝ እንደገለጸዉ ከሆዷ ያወጡት ህጻን ለተወሰነ ጊዜ ነፍሱ አልወጣችም ነበር ። ይህንን የሰማዉ ሕዝብ እጅጉን ተደናገጠ ። የግድያዉ ዜና እንደ ሰደድ እሳት ተዳረሰ ። የዜናዉን ተዐማኒነት የተጠራጠሩ ወገኖች የተወራዉ ዉነት መሆኑን በገዛ ዐይኖቻቸዉ አይተዉ ለማረጋገጥ ወደ ግድያዉ ሥፍራ ጎረፉ።

በዚያን ቀን የተካሄደዉ ግድያ የዳሮ ብቻ አልነበረም ። ቅድስት ማርያም ካቴድራል አጠገብ አንድ መነኩሴ ፤ የድሮዉ አዉሮፕላን ማረፊያ አጠገብ ሦስት ሠራተኞች ፤ ሰበታ አካባቢ አምስት ሰዎች ፤ በተለያዮ አካባቢዎችም በርካታ ዜጎች ተገድለዋል ። አገዛዙ ያሰማራቸዉ ነፍሰ ገዳዮች ያሻቸዉን አድርገዉ አምሮታቸዉን በመወጣት ተጠምደዉ የዋሉበት ልዩ ቀናቸዉ ነበር ። በዚያኑ ዕለት ግንፍሌ ድልድይ አጠገብ አራት መምሕራን መገደላቸዉንና ሬሳቸውም በአንድ በመስኖ በለማ አነስተኛ የአታክልት ሥፍራ እንደተጣለ ሰማሁ ። በፍርሀት እየተንዘፈዘፍኩ ወደተባለዉ ሥፍራ በጥድፊያ አመራሁ ። ከተገደሉት መሃከል አንደኛዉ የመጀመሪያ መጠለያዬ የነበረዉ ቤት ባለቤት የሆነዉ መምሕር መሆኑን ተረዳሁ ። የፊቱን ገጽታ አይቶ መለየቱ በፍጹም አዳጋች ነበር ። ሆኖም በለበሰዉ ፤ ሽክላማ ቀለም በነበረዉና የሚስቱ የእጅ ሥራ በሆነዉ ሹራብ ለየሁት ።

እነዚህን መሰል ፖለቲካዊ ግድያዎች የሕዝቡን የቁጣ ጩኸት ቀሰቀሱ ።ገዳዮቹ ደግሞ በነዋሪዉ ዘንድ የማይታወቁ አልነበሩም ። ነፍሰ ገዳዮቹ ታጣቂዎች በጉራ የተወጠሩ ጀብደኞች፤ ያለአንዳች ማንገራገርና የጎሊና ወቀሳ የፈለጉትን ሰዉ ተኩሰዉ የሚገድሉ ናቸዉ ። ቀዉሱ ግርማ ከበደና በርሱ የሚመሩት ነፍሰ በላዎች አራት ኪሎ አካባቢ በዳሮ ነጋሽና በሌሎቹም ላይ ለተፈጸመዉ ግድያ በቀጥታ ተጠያቂ ናቸዉ ። በሰዉ ስቃይ የሚደሰቱት እነዚህ አረመኔዎች ፤ ገደብ ባልነበረዉ ግብረ ሽብራቸዉ ወታደራዊዉን መስተዳድር ለከፋ ትችት አጋለጡት ። በዚህም ሳቢያ በስተፍጻሜዉ ፤ ለጥፋት አስታጥቆ ባሰማራቸዉ አገዛዝ አላዉቃችሁም ሊባሉ በቅተዋል ።

ይቀጥላል........